# የአስር ቀንና ወርሃዊ የአየር ሁኔታና ጠባይ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከጁላይ 21-31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከኦገስት 1-10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2022
አዲስ አበባ

| ርዕስ | ገፅ |
| --- | --- |


እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ 1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ........ 2

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት........ 3

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ........ 4

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር........ 4

እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ........ 5

በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ........ 5

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 5

እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 6

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 6

እ.ኤ.አ ከኦገስት1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር........ 7

ሁኔታ አዝማሚያ........ 7

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10, 2022 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ........ 8

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 8

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 9


## እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት ለወቅቱ ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ተጠናክረዉ የነበረ ሲሆን፤ ዝናቡ በመጠን ረገድ በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አንፃራዊ ጥንካሬ አሳይቷል፡፡ በተመሳሳይ በሌሎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይም የተለያየ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአንድ ቀን ከ30 እስከ 117.9 በሚ.ሜ የደረሰ ከባድ የዝናብ መጠን በብዙ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች ላይ ተመዝግቧል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ በምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ በደቡብ ደጋማና በምስራቅ ኦሮሚያ፣ በሰሜን ሶማሌ፣ በሐረሪና ድሬዳዋ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ በሲዳማና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንዲሁም አፋር ክልሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ባለፉት አስር ቀናት ከ1 - 3 ቀናት ያህል ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል በደባርቅ 41.2ና 36.9፣ በጎንደር 39.2ና 54.1፣ በባህር ዳር 37.3ና 117.0፣ በሲሪንቃ 41.5፣ በባቲ 91.5ና 32.0፣ በደብረወርቅ 57.3፣ በካቺስ 60.4፣ 31.4ና 44.4፣ በጅማ 52.0ና 44.8፣ በወሊሶ 37.3፣ 40.0፣ በነቀምቴ 117.9 እና በሆሳዕና 43.8 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤንሻንጉል፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሁሉም ዞኖች፣ በወለጋ ሁሉም ዞኖች፣ በቡኖ በደሌ፣ በኢሉ አባቦራ፣ በጅማ፣ በሰሜን ሸዋ(04)፣ በደቡብ ምዕራብና ምዕራብ ሸዋ፣ በአዲስ አበባ፣ በጉራጌ፣ በስልጤና ሀዲያ፣ ከአፋር ክልል በዞን 02፣ 04፣ 05ና 03 ላይ ከ50-315 ሚሜ የሚደረስ በአብዛኛዉ ከ4-11 ቀናት ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በተቀሩት የአፋር እና የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንዲሁም የሲዳማ ክልል ክልል ዞኖች፣ በምስራቅ ሸዋ፣ በምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ በአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ በባሌና በጥቂት የጉጂ ዞን፣ በፋፈንና ሲቲ ዞኖች ላይ ከ5-50 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4 ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ
(ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤንሻንጉል፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በቡኖ በደሌ፣ በኢሉ አባቦራ፣ በጅማ፣ በሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ በጥቂት የጉጂና ቦረና፣ በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በሀዲያ፣ በጎፋና በደቡብ ኦሞ እንዲሁም በአፋር ክልል ከሞላ ጎደል ሁሉም ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸዉ
(ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3   እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




የወቅቱን ዝናብ የማያገኙ አካባቢዎች

ከመደበኛ በታች


መደበኛ

ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የመጨረሻው የጁላይ አስራ አንድ ቀናት ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የተሻለ ጥንካሬ የነበራቸው ሲሆን፤ በተለይም በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ጠንከረ ያለ የእርጥበት ሁኔታ ተስተውሏል። ሆኖም ግን በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች ላይ በመጠን ይለያይ እንጂ በስርጭት ረገድ ብዙ ቦታዎችን ያዳረሰ የእርጥበ ትሁኔታ እንደነበራቸው ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም የተገኘው እርጥበት ለመኸር የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን፤ በተለይም የመካከለኛ ጊዜ የመኸር ሰብሎችን ለመዝራትና የማሳ ዝግጅት ለማከናወን እንዲሁም በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀደም ብለው ለተዘሩ ለረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎችና ለተለያዩ የጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር ልምላሜ ጥሩ አስተዋጽኦ የነበረው ከመሆኑም በላይ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበት አንፃር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በአንፃሩ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድና ተከታታይነት የነበረው የዝናብ ሁኔታ ለወንዝ መሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ የጎርፍ መከሰት ያስከተለ ሲሆን፤ እንዲሁም የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት እንዲኖር አድርጓል (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በአብዛኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ እንዲሁም ስምጥሸለቆ፣ የላይኛዉና የመካከለኛዉ ተከዜ፣ አዋሽ፣ የላይኛዉ ዋቤ ሸበሌ እና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም ከእርጠበታማ እስከ መጠነኛ እርጥበት የተሰተዋለባቸው ተፋሰሶች በታችኛው ስምጥሸለቆ፣ በጥቂት የላይኛው ዋቤ ሸበሌ ገናሌዳዋ እንዲሁም በመካከለኛው አዋሽ ተፋሰሶች ይገኙበታል ፡፡ በተቀሩት በአብዛኛው የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በከፊል ደረቅና ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተሰተውሏል (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከኦገስት1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በኦገስት የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ከፍሎች ላይ ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በዚህም መሰረት በቀጣዩ አሥር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ዝናቡ በተጠናከረና በተስፋፋ ሁኔታ ቀጣይነት ሊኖረዉ እንደሚችል እንዲሁም የሰሜን፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብ እና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት የሚኖራቸዉ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በመሆኑም ከሚጠበቀዉ የተጠናከረ የዝናብ ሁኔታና ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ ዝናብ እያገኙ ባሉት የተለያዩ አካባቢዎች በተለይም በተዳፋትና በወንዞች ዳርቻ አካባቢ ጎርፍ ሊከሰት ስለሚችል ህብረተሰቡና የሚመለከተዉ አካል ከወዲሁ ጥንቃቄ እንዲያደርግ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ያሳስባል፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ሁሉም የወለጋና የሸዋ ዞኖች፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ እና ቡኖ በደሌ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ዙሪያ፤ አዲስ አበባ፤ ሁሉም የአማራ ክልል፤ የቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ የጋምቤላ ክልል እና ሁሉም የትግራይ ዞኖች፤ ሁሉም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና የሲዳማ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ደግሞ ዞን 3፣ 4 እና ዞን 5፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የሀድያ፣ የጉራጌ፣ የስልጤ፣ የወላይታ ዞኖች አብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊከሰት ይችላል፡፡ ከዚህም ሌላ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ ዞኖች፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ጥቂት የምስራቅ ሐረርጌ እና የሰሜን ቦሌ ዞኖች፣ እንዲሁም ድሬዳዋ እና ሀረሪ፤ የጋሞና የጎፋ እንዲሁም የጌዲ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 1 እና 2፤ ከሶማሌ ክልል ሲቲ ዞን፤ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ቦታዎች በአብዛኛው ደረቃማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ (ካርታ 6) ፡፡

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1-10, 2022 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.




## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኦገስት ወር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በሁሉም የወቅቱ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ዝናቡ ቀጣይነት እንደሚኖረውና በተለይም የሰሜን፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብ እና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት የሚኖራቸዉ ሲሆን አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ከባድ ዝናብ እንደሚኖርና ከዚሁም ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የእርጥበት ሁኔታው ይበልጥ የተጠናከረ ሊሆን እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ አስቀድመው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም የመኸር ወቅት እርሻ እንቅስቃሴን ዘግይተው ለጀመሩ አካባቢዎች የአፈር ውስጥ እርጥበትን እንደሚያሻሽልና ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት እና በአሁኑ ጊዜ እርጥበት በማግኘት ላይ ለሚገኙት በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ሊኖር የሚችለው እርጥበት በአካባቢው ለሚገኙት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሮች የግጦሽና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦትን ለማሻሻል የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በሌላ በኩል ከመደበኛ በላይ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ አካባቢዎች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ እርጥበቱ ከመጠን በላይ ሊሆን ሰለሚችል በዚህም ምክንያት

ውሃ ማሳ ላይ እንዳይተኛ ቦይ በማውጣት፣ የማንጣፈፍና የመከላከል ስራ በመስራት እንዲሁም አረምን በወቅቱ በማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱ ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ከሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ ቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት በተለይም በተከታታይ ዝናብ እያገኙ ባሉ እና ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸው ቦታዎች አርሶ አደሩ እና የሚመለከታቸው አካላት በጋራ በመሆን በሰብሎች፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የእርጥበት ስርጭትና መጠን የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የተጠናከረ የእርጥበት መጠንና ስርጭት እንደሚኖረው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህም መሰረት በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ አዋሽ፣ አፋርደናከል፣ የላይኛውና የመካከለኛው ስምጥሸለቆ እንዲሁም የላይኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እስከ በጣም ከፍተኛ የእርጥበት መጠን የሚያገኙ ሲሆን፤ በእነዚህ ተፋሰሶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ የከባድ ዝናብ ክስተት ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም የላይኛው ገናሌዳዋ፣ የታችኛው ኦሞጊቤ እንዲሁም መካከለኛው ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ከመጠነኛ እስከ እርጥበታማ  እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ይህንን ተከተሎ ከላይ በተጠቀሱት ከከፍተኛ እስከ በጣም ከፍተኛ የእርጥበት መጠንና ስርጭት የሚኖራችው ተፋሰሶች ላይ የሚከሰተው ዝናብ በተዳፈት ቦታዎች ላይ መሬት መንሸራተት፣ የወንዞችና የውሃ ማጠራቀሚያዎች ሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ አካባቢዎች ላይ ደግሞ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊስከትል ስለሚችል በእነዚህ ቦታዎች ላይ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊውን ክትትልና ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች ደረቅና ከፊል ደረቅ ሆነዉ ይቆያሉ።